## የአሥራ አራት ዓመታት ድርድር፣ አንድ ሺህ አምስት መቶ ስብሰባዎች

ታሪክ እንደሚነግረን ኮሪያ ከ1910 እስከ 1945 ድረስ በጃፓን ቅኝ አገዛዝ ሥር ቆይታለች። 40 ዓመታት ያህል በቆየው በዚህ የቅኝ ግዛት ዘመን ጃፓን በኮሪያውያን ላይ ተነግሮ የማያልቅ ግፍ ፈጽማለች። እንደሚታወቀው ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ኮሪያ አንድ አገር ነበረች። ሰሜንና ደቡብ ኮሪያ የሚባሉ ሁለት አገራት የተፈጠሩት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። እናም ጃፓን በቅኝ ግዛት ይዛ የነበረው ሁለቱንም ኮሪያዎች በአንድነት ጠቅልላ ነበር። የጃፓን ንጉሳዊ መንግሥት ኮሪያን በቅኝ ግዛት በያዘበት ወቅት በሁሉም የኮሪያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በኮሪያ ቋንቋ ትምህርት እንዳይሰጥ ከለከለ። ከዚያም የኮሪያን ሕዝብ የዘመናት የሥልጣኔ አሻራዎች የሚያሳዩ የታሪክ ሰነዶች በሙሉ ከያሉበት ተሰብስበው እንዲቃጠሉ አደረገ። ይህም ሳይበቃ የጃፓን ቅኝ ገዢዎች የኮሪያን አገር በቀል ዛፎች በመጨፍጨፍ ከጃፓን በመጡ የዛፍ ዝርያዎች እንዲተኩ አድርገዋል። ይህም ሳይበቃ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኮሪያ ዜጎች በኃይል ተገደው መጠሪያ ስማቸውን እንዲቀይሩ ተደርገዋል። በቅኝ ግዛቱ ዘመን 84 ከመቶ የሚሆኑት ኮሪያውያን በግዳጅ ስማቸውን እንዲቀይሩ ተደርጓል። በሌላ በኩል በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኮሪያውያን በኃይል ወደ ጃፓን እና በጃፓን አገዛዝ ሥር ወደ ነበሩ ግዛቶች ተግዘው አሰቃቂ የሆነ ነጻ የጉልበት ሥራ እንዲሰሩ ተደርገዋል። በዚህም ብዙዎቹ በበሽታና በምግብ ዕጦት አልቀዋል። ኮሪያውያን በጃፓን ቅኝ ገዢዎች ባህላቸውንና የሥልጣኔ አሻራዎቻቸውን ለማጥፋት የተደረገባቸውን የግፍ ዘመቻ Cultural Genocide ብለው ይጠሩታል።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ ኮሪያም ከጃፓን የግፍ አገዛዝ ነጻ ወጥታለች። ይሁንና ከነጻነቱ በኋላ ከ1950 እስከ 1953 ለሦስት ዓመታት በኮሪያውያን መካከል በተካሄደው ደም አፋሳሽ የእርስ በርስ ጦርነት ሰሜንና ደቡብ ኮሪያ የተባሉ ሁለት አገራት ሊፈጠሩ ችለዋል።

ጃፓን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተሸነፈች በኋላ በጦርነቱ ወቅትና ቀደም ባሉት ዓመታት ግፍ ከፈጸመችባቸው አገራት ጋር እርቅ ለማውረድና ወዳጅነት ለመመስረት ቆርጣ ተነሳች። እርቁን ለማሳካት አዲሶቹ የጃፓን መሪዎች ያደረጉት ትልቅ ነገር አባቶቻቸው የፈጸሙትን ግፍና በደል አምነው መቀበልና ይቅርታ መጠየቅ ነበር። በዚህም አዲሶቹ መሪዎች በጦርነቱ ወቅት በጃፓን ግፍ የተፈጸመባቸውን አገራት ከወገባቸው ዝቅ እያሉ ይቅርታ ጠይቀዋል። ጃፓን በኢኮኖሚ እየጠነከረች ስትመጣም ጉዳት ለደረሰባቸው አገራት የገንዘብ ካሳ ጭምር በመክፈል እርቅ አውርደዋል።

ታዲያ ለአዲሶቹ የጃፓን መሪዎች እጅግ አስቸጋሪ የነበረው ከደቡብ ኮሪያ ጋር ያደረጉት የእርቅ ሂደት ነው። የተፈጸመው በደል እጅግ የከፋ ስለነበር እርቁንም በዚያው ልክ ከባድ አድርጎታል። ጃፓኖች ግፍ ያደረሱት በሁለቱም ኮሪያዎች ላይ ቢሆንም ሰሜን ኮሪያ አስቀድማ በሯን በመዝጋቷ አሁንም ድረስ ከጃፓን ጋር ገና አልታረቀችም። የጃፓን መሪዎች በሰሜን ኮሪያ ላይ ተስፋ በመቁረጣቸው እርቁን ከደቡቡ ጋር ብቻ ለማድረግ ወሰኑ። ጃፓኖች ከደቡብ ኮሪያ ጋር ለመታረቅ ለ14 ዓመታት የቆየ እልህ አስጨራሽ ዲፕሎማሲ [ድርድር] አካሂደዋል። የሁለቱ አገራት ተደራዳሪዎች በ14 ዓመታት ውስጥ 1500 መደበኛ ስብሰባዎችን ካካሄዱ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1965 ለመታረቅ በቅተዋል። እርቅ ከወረደ በኋላ ከፉው ዘመን ባይረሳም ታሪክ ሆኗል። አሁን ጨዋታው ንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ነው። ዛሬ ላይ በመካከላቸው ያለው የንግድ ልውውጥ አንድ መቶ ቢሊዮን ዶላር ዘሏል። የደቡብ ኮሪያ ወጣቶች ለሸርሸር የሚመርጡት አገር ጃፓንን ነው። የጃፓኖቹም እንዲሁ። በ2023 ብቻ ሰባት ሚሊዮን የደቡብ ኮሪያ ቱሪስቶች ጃፓንን ጎብኝተዋል። በተጨማሪም በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ የደቡብ ኮሪያ ወጣቶች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ጃፓን እየጎረፉ ነው። ከዚያም አልፎ ሁለቱ አገራት የ2002ቱን የዓለም ዋንጫ በጋራ ለማዘጋጀት በቅተዋል። የሁለቱም አገራት የእግር ኳስ ቡድኖች ለዋንጫው ባይደርሱም መስተንግዷቸው ድንቅ ነበር ተብሏል። መቸም ዲፕሎማሲ የማይፈታው ችግር የለም።

**የጃፓን መንገድ**

**ቋሚ ጥቅም እንጂ ቋሚ ጠላት የለም**

ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ።

ደራሲ........ አሰፋ ማመጫ አርጋው

መጽሐፉ በጃዕፈርና በሌሎችም መጻሕፍት ቤቶች ይገኛል።